# ጥላሁን ገሠሠ



"እንኳንስ ዘፈኑ ያስደስታል መልኩ
ምንም አልተገኘም ለጥላሁን ልኩ" - ገዛኸኝ ደስታ 1955 ዓ.ም.
እስካሁንም የለም የሚሆን ምትኩ።

በተፈጥሮ በታደለው ድምጹ፣ የስንታችንን ስሜት እየሰረቀ ገሚሶቻችንን እያስለቀሰ፣ ሌሎቻችንን ደግሞ በፍቅርና በትዝታ እያስኳዘን ከ50 ዓመታት በላይ ኢትዮጵያውያንን ሲያዝናና የነበረው፣ አንጋፋው ድምጻዊ ጥላሁን ገሠሠ በሞት ስለተለየን፤ የዚህን ባለሙያ ውለታ ለማስታወስና በኪነት ሙያው ስላደረገው አስተዋጽኦ በማክበር፤ በሲያትል የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማሕበር፤ በመጪው እሁድ ኤፕሪል 26 ቀን ከቀትር በኋላ 5 ፒ ኤም ሻማ እየተበራ፤ የህይወት ታሪኩ በአጭሩ እየተነገረ ይታወሳል።

ይህ ድምጻዊ የኪነት ሰው፤ ቁጥራችን በዛ የሚለው ኢትዮጵያውያን የርሱን ዜማዎች እየሰማን ያደግን ስለሆነ፣ በልባችን ውስጥ ልዩ ስፍራ አለው። ስለዚህም የምነረሳው አይደለም።

እነሆ ሞት ለማናችንም የመጨረሻ ጽዋችን መሆኑን ባንረሳም፣ የምንወደውን ከጎናችን ስናጣው፣ ልዩ የሐዘን ስሜት በልቦናችን ስለሚቀረጽ፣ ሁላችንም ተሰባስበን፣ ስሙን በአንክሮ አንስተን፣ ስለሕይወቱ ማለፍ የሚገባውን ከበሬታ አሳይተን ያበረከተውን ሥራ አድንቀን፣ እንድንሰናበተው ጥሪውን ለሁላችሁም በትህትና እናቀርባለን።

ከከበረ ሰላምታ ጋር

በሲያትል የኢትዮጵያውያን መረዳጃ ማሕበር
አድራሻው፤

2301 South Jackson Street, Suite 103
Seattle WA 98144 Phone (206) 325 0304